## የምን ወዬ ወዬ!

የምን ወይኔ ወይኔ፣ የምን ወዬ ወዬ፣
መለስ ሁሉን ንቆ ዘር እያደባዬ።
«ይሄ ዝም ማለት ለበግም አልበጃት፣
ሃምሳ ነብሷን ሆና አንድ ነብር ፈጃት።»
የሚለው ተረት ነግ - በኔ ነውና፣
እራስህን አድን ምክንያት ተውና።

ምርጡ የመለስ ዘር በጥጋብ ሲያገሣ፣
አንተ ተቸግረህ ስትበላ ቂምሣ፣
ሁለተኛ ዜጋ መሆንክን አትርሣ፣
ይህ ሁሉ አንገፍግፎህ መርሮህ ባትነሣ፣
ለልጅ ልጅ መተውክን የታሪክ ጠባሣ፣
ከቶ ለደቂቃም ጭራሽ እንዳትረሣ።
እምብኝ አሻፈረኝ፣ በቃኝ ውረድ በለው፣
በጭነቱ ብዛት ቆስሎ የተላጠው፣
እስከመቼ ድረስ ገጣባህ ይቻለው?

የሰካራም ስድብ ሰካራም እንዲሉ፣
የወያኔም ስድብ «አሸባሪ» ሆኗል፣ የጠላውን ሁሉ።
የወያኔ ቅዠት ተኝቶም በቁሙ፣
ከሽብር በስተቀር የሚታየው የለም፣ ብዙሪያ ጥምጥሙ።

የእነ- አንዱ ዓለም ልሣን፣ በጣም የተሳለው፣
የእነ - እሥክንድር ብዕር ወግቶ የሚጥለው፣
በእሥራት አይጠፉም፣ ረመጥ እሣት ነው።

የወያኔን ቅጥፈት፣ የወያኔን ሤራ፣
በግልጽ በማጋልጥ፣ በሕዝቡ ምካከል መንፈስ ስለዘሩ፣
እኒያ ታላቁ ሊቅ የተባሉት አንቱ፣
ሕገ - አራዊትን ቀድምው እንዳተቱ፣
እሥክንድር - አንዱዓለም፣ በሽብር ታገቱ!?
የአራዊቱ መንገድ ታዬ ቁልቁለቱ።

ልብሱን ጥሎ አበደ፣ ወያኔ ለየለት፣
ስም እየለወጠ ጀመረ መሚገት።
አንዱዓለም አሸብር፣ እሥክንድር አሸብር፣
እያለ ጠራቸው ጨንቆት ሲንጸረጸር።

የሰላሙ ታጋይ አንዱዓለም አራጌ፣ ቆፍጣናው ቆራጡ፣
የሠላም ተሟጋች ጀግና እሥክንድር ነጋ፣ የሣት ረምጡ፣
ነብር መች ይድክማል ጅራቱን ቢቆርጡ።
የመለስ ጀሌዎች ይሠሩትን ያጡ፣
ክመሄድ በስተቀር ከድጥ ወደማጡ፣
ታጋይን በማሠር መፍትሄ ላይሰጡ፣
ታጋይ ቢሞት እንጅ፣ ትግል ስለማይሞት ክንቱ አይራወጡ።

እሥክንድር ብዙ ነው፣ አያልነው አንዱዓለም፣
የተገፋው ሁሉ ከእነርሱ አይለይም።

አሸብር ከሆነ የተገፋው ሁሉ፣
ሸብር ነው ማለት ነው አገሩ በሙሉ፣
ቀውስ ወያኔዎች ትንሽ ቆም ብለው ነገን ያስታውሉ፣
እሣተ - ገሞራው መፈንዳቱ አይቀርም በምን ይመርጋሉ?
ምን መሬት ቢሸጡ ምን ቤዝ ቢዋዋሉ፣
ድሮን አያድኑም ዜጎች በቃኝ ሲሉ።
የመለስ ምልምሎች ሆድ - አደሮች ሁሉ፣
ያች ቀን ስትደርሥ ከምን ይጠጋሉ?
ጎበዝ አንድ እንሁን አትከፋፈሉ፣
ጠላትን እንደ እህል ለነገ አትበሉ።

«ነካካቸው አትስጣቸው ጤና፣
ምንጊዜም ደህና -ሰው አልተባልክምና!»

ከበላቸው አሸብር
(መሥከረም 2004 ዓ.ም.)